ዐውደ ነዋይ

ቅፅ 01 ቁ.1፤ ጥቅምት 2017 ዓ.ም

ዲጅታል ቅጂ

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
Commercial Bank of Ethiopia

ዲጅታል ባንክ - ለመጪው ጊዜ

ማውጫ

የአዘጋጁ መልዕክት	3
አበይት ክንውኖች	4
ባንክ አገልግሎት የሲቢኢ ብር ፕላስ	7
ባንክ ቴክ ዲጅታል ባንክ - ለመጪው ጊዜ!	10
መዝናኛ አገር ወካዮች መፍለቂያ፣ ሻምፒዮናነት መድመቂያ!	14
ፎቶ ማህደር	18

በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን በየሩብ ዓመቱ የሚታተም

አድራሻ፡- አዲስ አበባ፣ ቂርቆስ ክከተማ፣
የቤት ቁ.፡- አዲስ፤

ኢሜል:- alsenassefa@cbe.com.et

ዋና አዘጋጅ

አልሰን አሰፋ

ም/ዋና አዘጋጅ

ብርሃኑ ኃይሉ

አዘጋጆች

ማርታ ዘሪሁን
ምንተስኖት አስቻለው
ተመስገን ዳምጠው
ኦሊቃ በላይ
ዋስይሁን ፈቃደ
ደረጀ ጌታሁን
ፀጋዬ ደስታ

ፎቶግራፍ

ዳግም ጌታቸው

አርታኢ

አስቻለው ተክሉ
ምንተስኖት አስቻለው

ሕትመት ክትትልና ስርጭት ቡድን መሪ

ተፈሪ ጋሞ

ሌይአውትና ዲዛይን

አብርሃም ውለታው

ምስል ክምችት ባለሙያ

ነብዩ እሸቴ

የአዘጋጁ መልዕክት

ባሳለፍነው ሩብ ዓመት ዓለም አቀፍና አገር አቀፍ በርካታ ኩነቶች ተስተናግደዋል፡፡ በአገራችን ከተከሰቱ ኩነቶች መካከል የመንግስት የማይክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ የፖሊሲ ለውጥ በዋነኛነት ተጠቃሽ ነው፡፡ ይህንኑም ተከትሎ በአገር ውስጥ ባንኮች አሠራር ላይ ለውጦች ታይተዋል፡፡

ባንካችን በመጀመሪያው ሩብ ዓመት አፈጻጸም ከዚሁ የማሻሻያ ፖሊሲ ጋር ተያይዞ የአሠራር ለውጦችን አድርጓል፡፡ አስፈላጊነታቸው ታምኖበት የአሠራር ለውጥ በተደረገባቸው የባንኩ አገልግሎቶችና የሥራ ሂደቶች የተስተዋለው አፈጻጸምም አበረታች ነው፡፡

በሌላ በኩል በሩብ ዓመቱ በዕቅድ የተያዙ የሀብት አሰባሰብ፣ የውጭ ምንዛሬ ግኝት፣ የዲጅታል ባንክ አገልግሎትና ተደራሽነት፣ የብድር አቅርቦትና አሠባሰብ፤ እንዲሁም ሌሎች ተግባራት ላይ የታየው የተሻለ አፈጻጸም በቀሪዎቹ ሩብ ዓመታት ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባዋል፡፡ ለዚህም ሁላችንም በትብብርና በጋራ መሥራት ይጠበቅብናል፡፡

‹‹ዐውደ ነዋይ›› ዜና መዋዕላችን በ2024/25 በጀት ዓመት የመጀመሪያውን የሩብ ዓመት የባንካችንን ዋና ዋና ተግባራትን በማካተት ቀርቧል፡፡

የ‹‹ዐውደ ነዋይ›› ዋና ዓላማ በየሩብ ዓመቱ የሚከናወኑ ተግባራትን በተመለከተ ለሁሉም የባንካችን ሠራተኞችና አጋሮች መረጃ ተደራሽ ማድረግ ነው፡፡ እንዲሁም በባንካችን የተለያዩ ክፍሎችና ዲቪዥኖች መካከል መልካም ተሞክሮዎችን ለመለዋወጥ ዕድል ይፈጥራል፡፡ በተጨማሪም የባንካችንን ዋና ዋና ኩነቶች ሰንዶ ለማስቀመጥ ከማስቻሉም ባሻገር በባንካችን ዙሪያ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ለሚያከናውኑ ተመራማሪዎች እገዛ ያደርጋል፡፡

‹‹ዐውደ ነዋይ›› በዲጅታል መልክ ተዘጋጅቶ በየሩብ ዓመቱ በዲጅታል መንገድ የሚሠራጭ ነው፡፡ የመጀመሪያው ዕትም ከመሆኑ ጋር በተያያዘ በአነስተኛ ኮፒ በማተሚያ ቤት ታትሞ ተሠራጭቷል፡፡ ይህን ያደረግነው ዜና መዋዕሉን ለማስተዋወቅ ዕድል ይፈጥራል ብለን በማሰብ ነው፡፡

በቀጣይ ዕትሞች የባንካችን ሠራተኞች መረጃዎችን፣

አልሰን አሰፋ
ዳይሬክተር - ኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን

ምስሎችን፣ እና ሐሳቦችን በማቅረብ እንድትሳተፉ እንጋብዛለን፡፡ በዲጅታል መልክ የሚሠራጨውን ኮፒ በማንበብ ይጠቅማል፤ ሊስተካከል ይገባዋል የምትሉትን አስተያየት ላኩልን፡፡ የዜና መጽሔቱ ዓላማ እንዲሳካ፣ ቀጣይነት እንዲኖረው፣ እና በጥራት እንዲዘጋጅ የባንካችን ማኅበረሰብ አባላት ተሳትፎ ወሳኝ ነው።

በመጨረሻም ይህንን የመጀመሪያ ዕትም ለፍሬ ላበቁት የኮርፖሬት ኮምዩኒኬሽን ባልደረቦች ምስጋና አቀርባለሁ።

መልካም ንባብ!

አልሰን አሰፋ
ዳይሬክተር - ኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና ቪዛ ኢንተርናሽናል በትብብር ለመስራት ተስማሙ

በዋስይሁን ፊቃደ

ዓለም ዓቀፍ ክፍያዎችን በቴክኖሎጂ በመታገዝ ለማከናወን የሚያስችለውን የትብብር ስምምነት ከቪዛ ኢንተርናሽናል ጋር መፈጸሙን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አስታወቀ፡፡

ስምምነቱን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፕሬዚዳንት አቶ አቤ ሳኖ እና የቪዛ ኢንተርናሽናል የምስራቅ አፍሪካ ምክትል ፕሬዚዳንት እና ዋና ዳይሬክተር ሚስተር ቻድ ፖሎክ ተፈራርመዋል።

ስምምነቱ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዋና መስሪያ ቤት መስከረም 10 ቀን 2017 ዓ.ም. ተከናውኗል፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፕሬዚዳንት አቶ አቤ ሳኖ በሥነ-ሥርዓቱ ላይ እንደገለጹት የትብብር ስምምነቱ ለባንኩ ስትራቴጂክ ጥቅም ያስገኛል፡፡ የውጭ ምንዛሪ ግብይት ተመን በገበያ ሥርዓት እንዲመራ መንግስት በወሰነው ውሳኔና የፖሊሲ ማሻሻያ መሠረት ዓለም አቀፍ ክፍያዎችን ለመፈጸም ወሳኝ ድርሻ ይኖረዋል፡፡ የባንኩን አሠራር ለማሻሻልም አስተዋጽኦ ያበረክታል ብለዋል፡፡

የቪዛ ኢንተርናሽናል ም/ፕሬዚዳንት እና የምስራቅ አፍሪካ ዋና ሥራ አስኪያጅ ቻድ ፖሎክ በበኩላቸው ቀደም ሲል ከባንኩ ጋር በተለያዩ ዘርፎች በትብብር ሲሰሩ መቆየታቸውን አንስተው፣ ደስተኛ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡ ድርጅታቸው ከባንኩ ጋር ያለው አጋርነት ከአገር ውስጥ የባንክ ሥራ መቀላጠፍ ባሻገር በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሚኖር የገንዘብ እንቅስቃሴ አጋዥ ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ቪዛ ኢንተርናሽናል እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያደረጉት ስምምነት ለአምስት ዓመታት የሚቆይ ሲሆን፣ ቪዛ ካርድን ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ደንበኞች ለማቅረብ እና ለባንኩ ሠራተኞች የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎችን ለመስጠት እንደሚያስችል ለማወቅ ተችሏል፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የአቢሲኒያ የኢንዱስትሪ ሽልማትን አሸነፈ

የባንኩ ፕሬዚዳንት አቶ አቤ ሳኖ በከፍተኛ አመራሮች ዘርፍ የዳይመንድ ደረጃ ኒሻን ተሸላሚ ሆነዋል

በኦሊቃ በላይ

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የአቢሲኒያ የኢንዱስትሪ ሽልማት የዳይመንድ ደረጃ ልዩ የዋንጫ ተሸላሚ ሆነ፡፡

በአዲስ አበባ ኢንተርሌግዠሪ ሆቴል ሐምሌ ወር ውስጥ በተካሄደ ሥነ- ሥርዓት ላይ ሽልማቱን ተረክቧል፡፡

በኢትዮጵያ ምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴ ላይ ስኬታማ ተሳትፎ ላደረጉ ተቋማት እና አመራሮች ሽልማት የሚያበረክተው አቢሲኒያ የኢንዱስትሪ ሽልማት ድርጅት፣ ከ75 ዓመታት በላይ የአገልግሎት ቆይታ ላላቸው እና በቆይታቸው ለተከታታይ ጊዜ ትርፋማ እና ስኬታማነትን ላስመዘገቡ ተቋማት እና ተቋማቱን በብቃት ለመሩ አመራሮች የሚሰጠውን ሽልማት ነው ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና ለባንኩ ፕሬዚዳንት አቶ አቤ ሳኖ የሰጠው፡፡

የባንኩን ፕሬዚደንት በመወከል በመርሀ ግብሩ ላይ የተገኙት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሰው ኃይል ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ ኤፍሬም መኩሪያ ከአቢሲኒያ የኢንዱስትሪ ሽልማት የበላይ ጠባቂ ከሆኑት የቀድሞ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ እጅ ሽልማቱን ተረክበዋል፡፡

አቶ ኤፍሬም በሥነ - ስረዓቱ ላይ እንደተናገሩት «ሽልማቱ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለሀገራችን የምጣኔ ሀብት ጉዞ እያበረከተ ያለውን ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚመሰክር ነው፡፡»

«እንዲህ አይነት ሀገራዊ ሽልማት ባንኩ በቀጣይ ለሚኖረው ሥራ ጥንካሬ ይሰጠዋል፡፡» ያሉት አቶ ኤፍሬም «ባንኩ ያለው ጠንካራ የሰው ኃይል ለባንኩ ስኬት መሰረት ነው፡፡» ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከ75 ዓመታት በላይ አገርን በማገልገልና በተከታታይ ትርፋማና ስኬታማ በመሆኑ የዳይመንድ ደረጃ ልዩ ዋንጫ ተሸላሚ መሆኑን በሥነ-

ስረዓቱ ወቅት ተገልጿል፡፡

የባንኩ ፕሬዚዳንት አቶ አቤ ሳኖ ለባንኩ ትርፋማነትና ስኬታማነት ባሳዩት ብቃት ያለው አመራር የ2016 ዓ.ም. የዳይመንድ ደረጃ ኒሻን እና ዕውቅና ተበርክቶላቸዋል፡፡

በአመራር ዘመናቸው የደንበኞችን አገልግሎት በማሻሻል፣ የፋይናንስ አካታችነትን በማስተዋወቅ እና ቴክኖሎጂን በመጠቀም ባንኩ በአገር ውስጥ መሪነቱን ለማስቀጠል እንዲችል አስተዋፅኦ ማበርከታቸው ለሽልማት እንዳበቃቸው አዘጋጆቹ ገልጸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በጋራ ለመስራት ተፈራረሙ

በዋስይሁን ፈቃደ

የፋይናንስ ዘርፉን ለማልማት በሚያስችሉ ተግባራት ዙሪያ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር በትብብር ለመስራት የሚያስችለውን የመግባቢያ ሰነድ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ተፈራረመ፡፡

ስምምነቱ በሁለቱም ወገኖች ሐምሌ 28 ቀን 2016 ዓ.ም. ተፈርሟል፡፡

የመግባቢያ ሰነዱ ሁለቱ ተቋማት በጥናት እና ምርምር፣ በሰው ሀይል ልማት፣ በቴክኖሎጂ እና ዲጂታል ዘርፍ፣ እንዲሁም የባንክና ፋይናንስ ዘርፉን በሚያግዙ የፈጠራ ስራዎች ላይ በጋራ ለመስራት ያስችላቸዋል ተብሏል፡፡

በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል ስምምነቱን የፈረሙት የፕሬዚዳንቱ ተወካይና የሰው ሀይል ም/ፕሬዚዳንት አቶ ኤፍሬም መኩሪያ በሥነ - ስረዓቱ ላይ እንደገለጹት ስምምነቱ ሁለቱ አንጋፋ ተቋማት በጋራ እና በትብብር እንዲሰሩ አቅም ይፈጥራል ብለዋል፡፡

‹‹ባለፉት ዓመታት ዩኒቨርሲቲው ለፋይናንሱ ዘርፍ ብቁ የሰው ሀይልን በማፍራት የላቀ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ አሁንም በማበርከት ላይ ይገኛል፡፡ በምርምር ስራዎች አይነተኛ ሚና እየተወጣ ያለ ተቋም በመሆኑ ከዩኒቨርሲቲው ጋር አብሮ መስራት እንደ አገር የምናበረክተውን አስተዋጽኦ ከፍ ያደርገዋል፡፡›› ሲሉ ተናግረዋል አቶ ኤፍሬም፡፡

የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ሳሙኤል ክፍሌ በበኩላቸው ዩኒቨርሲቲያቸው ከባንኩ ጋር በጋራ ለመስራት የሚያስችለውን መግባቢያ ሰነድ መፈራረሙ ለፋይናንስ ዘርፉ መልካም አጋጣሚን ይፈጥራል ብለዋል፡፡

‹‹ባንኩ በዓለም አቀፍ ደረጃ በአገራችን ተወዳዳሪ የፋይናንስ ተቋማት እንዳሉ የምናሳይበት ተቋም በመሆኑ በትብብር መስራታችን ለዩኒቨርሲቲያችን ከፍ ያለ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡›› በማለት ገልጸዋል፡፡

የመግባቢያ ሰነዱ የተቋማቱን ትብብር የሚያጠናክር ሲሆን በፋይናንስ ዘርፍ የሚደረጉ ምርምሮችን ለማሳደግ እና ወደ ተግባር ለማሸጋገር ያስችላል ተብሏል፡፡

‹‹የሲቢኢ ኑር አገልግሎት በፍጥነት እያደገ ነው››

ሼህ መሐመድ አህመዲን (ዶ/ር)

በፀጋዬ ደስታ

የሲቢኢ ኑር አገልግሎት በየጊዜው መሻሻልና ፈጣን ዕድገት እየታየበት ነው ሲሉ የሼሪዓ አማካሪ ኮሚቴ ቦርድ ሡብሳቢ ሼህ መሐመድ አህመዲን (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

ባንኩ በአገልግሎቱ ዙሪያ ከደንበኞቹ ጋር በአጋሮ ከተማ ውይይት አካሂዷል፡፡

ሼህ መሐመድ አህመዲን (ዶ/ር) በውይይቱ ላይ እንደተናገሩት የሲቢኢ ኑር አገልግሎት በየጊዜው በፍጥነት እያደገና አገልግሎት አሰጣጡ እየተሻሻለ መጥቷል ብለዋል፡፡ በቀጣይም አገልግሎቱን ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግና የፋይናንስ አካታችነትን ለማረጋገጥ እየተሰራ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

ሼህ መሐመድ አህመዲን (ዶ/ር)
የሲቢኢ ኑር የሼሪዓ አማካሪ ኮሚቴ ቦርድ ሡብሳቢ

በውይይቱ ላይ የተገኙት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ደቡብ ምዕራብ ሪጂን ም/ፕሬዚደንት አቶ ሙሉነህ ለማ በበኩላቸው የሲቢኢ ኑር የፋይናንስ አገልግሎት በርካታ ደንበኞቹን ተጠቃሚ እያደረገ ነው ብለዋል፡፡ ደንበኞች የፋይናንስ አማራጮችን በመጠቀም በምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴ ላይ ያላቸውን ተሳትፎ እንዲያሳድጉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡ ባንኩም የደንበኞችን ፍላጎት ያስቀደመ አገልግሎት ለማቅረብ ቁርጠኛ መሆኑን ለውይይቱ ተሳታፊዎች ገልጸዋል፡፡

በውይይቱ ላይ በአጋሮና አካባቢው የሚገኙ የሲቢኢ ኑር ደንበኞች፣ የባንኩ የዋና መ/ቤት እና ጂማ ዲስትሪክት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎችና ጥሪ የተደረገላቸው ባለድርሻዎች ተገኝተዋል፡፡

‹‹የአካባቢ መራቆትን ለመከላከል የሚከናወኑ ሥራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ›› አቶ አቤ ሳኖ

በፀጋዬ ደስታ

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አመራሮችና ሠራተኞች የሚያከናውኗቸው የአካባቢ ጥበቃ ሥራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ ሲሉ ፕሬዚዳንቱ አቶ አቤ ሳኖ ተናገሩ።

በ2016 ዓ.ም አረንጓዴ አሻራ መርሐ - ግብር በባንኩ ሰራተኞች 311,500 ችግኞች ተተክለዋል፡፡

በአንድ ጀንበር ስድስት መቶ ሚሊዮን ችግኞችን ለመትከል የቀረበውን አገራዊ ጥሪ ተከትሎ የዋናው መ/ቤትና የአዲስ አበባ ዲስትሪክቶች በጋራ፣ በቦሌ ለሚ ኢንደስትሪ ፓርክ 20ሺ ችግኞችን ተክለዋል፡፡

በመርሐ - ግብሩ ላይ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፕሬዚደንት አቶ አቤ ሳኖ እንደገለጹት ባንካቸው የአካባቢ መራቆትን ለመከላከልና ማህበራዊ ሃላፊነቱን ለመወጣት የሚያከናውነውን ተግባር አጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

‹‹ለበርካታ ዓመታት የባንኩ አመራሮችና ሠራተኞች የችግኝ ተከላ መርሐ - ግብር ሲያከናውኑ ቆይተዋል፡፡›› ያሉት አቶ አቤ የተተከሉ ችግኞችን ለመንከባከብ ጠንክሮ ይሠራል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በዋናው መ/ቤትም ሆነ የባንኩ ዲስትሪክቶችና ቅርንጫፎች በሚገኙባቸው

የአገራችን አካባቢዎች የተካሄዱ የችግኝ ተከላ መርሐ - ግብሮች እንዲሳኩ ለተባበሩ ሠራተኞችና ባለድርሻ አካላትም ፕሬዚደንቱ ምስጋናቸውን አቅርበዋል፡፡ ወደፊትም ይኸው ትብብርና አጋርነት ሊቀጥል ይገባል ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያን ሕዝብ በማስተባበር በአገር አቀፍ ደረጃ የተከናወነው የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል አገራችን እየወሰደች ላለው ተጨባጭ እርምጃ ማሳያ እንደሆነ ይነገራል።

100 ሚሊዮን ብር ድጋፍ ተሠጠ

በኦሊቃ በላይ

ለመቄዶንያ የአረጋውያንና አዕምሮ ሕሙማን መርጃ ማዕከል የ100 ሚሊየን ብር ድጋፍ መስጠቱን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ገለፀ፡፡

የባንኩ ፕሬዚደንት አቶ አቤ ሳኖ በማዕከሉ በመገኘት ድጋፉን አበርክተዋል፡፡

ማዕከሉ የሚያከናውነው የበጎ ተግባር ሥራ የሚጠይቀውን ከፍተኛ ወጪ፣ እንዲሁም አገልግሎቱን ለማስፋት በማስገንባት ላይ ያለው ባለ 15 ወለል ህንፃ ወጪን ታሳቢ በማድረግ የገንዘብ ድጋፉ መደረጉን አቶ አቤ ገልጸዋል፡፡

ፕሬዚደንቱ ማዕከሉ እየሰጠው ባለው አገልግሎት ዙሪያ ገለጻ የተደረገላቸው ሲሆን፣ ከሥራ ባልደረቦቻቸው ጋር በመሆን በአልጋ ላይ ሆነው የሚደገፉ የማዕከሉን ተጠቃሚዎች ጎብኝተዋል፡፡

‹‹ማዕከሉ ከ7 ሺ 500 በላይ የሀገር ባለውለታ አረጋውያንና የአእምሮ ሕሙማንን ከወደቁበት አንስቶ መጠለያ በመስጠት እና በመንከባከብ እየሠራ ያለው ሥራ ሊመሰገን እና ሊደገፍ የሚገባው ነው፡፡›› ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ከዚህ ቀደም በተለያዩ ጊዜያት ለማዕከሉ ከ205 ሚሊዮን ብር በላይ ድጋፍ ማድረጉን ያስታወሱት አቶ አቤ፣ ወደፊትም ከማዕከሉ ጎን በመቆም ድጋፋቸውን እንደሚቀጥሉ ጠቁመዋል፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በጤናው ዘርፍ፣ በትምህርት፣ በአካባቢ ጥበቃ፣ በሰብአዊ ሥራ ድጋፍ እና በሌሎች ዘርፎች ማኅበራዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት ባለፉት አምስት ዓመታት ከ3 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር በላይ ድጋፍ አድርጓል፡፡

ዘመኑን የዋጀ የእጅ ስልክ ገንዘብ (Mobile Money) አገልግሎት

በደረጀ ጌታሁን

በ2017 ዓ.ም. መዳረሻ 3 ሳምንታት በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማዕከል ደማቅ የአዲስ ዓመት መቀበያ ኤክስፖ ሲካሄድ፣ የመግቢያ ቲኬት የተቆረጠው በሲቢኢ ብር አገልግሎት ብቻ ክፍያ እየተፈጸመ ነበር። ኤክስፖው ራሱም "ሲቢኢ ብር ፕላስ 2017 ኤክስፖ" ተብሎ ነበር የተሰየመው። የኤክስፖው ጎብኚዎች ደግሞ "ሲቢኢ ብር ፕላስ" የተሰኘውን የተሻሻለ የሲቢኢ ብር አገልግሎት መተግበሪያ በእጅ ስልካቸው ጭነው እንዲጠቀሙ እየታገዙ ነበር። ሐምሌ 18 ቀን 2016 ዓ.ም. ሥራ ጀምሮ በዚህ መልኩ ብዙ ሺህ ጎብኚዎች ዐውቀው እንዲጠቀሙበት የተደከመለት መተግበሪያ የሲቢኢ ብር አገልግሎትን ጠቀሜታ እና ደረጃ በእጅጉ ከፍ አድርጓል።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሞባይል ገንዘብ አገልግሎት በ2009 ዓ.ም. በተጀመረበት ወቅት አዲስ እንደመሆኑ መጠን በሚፈለገው ፍጥነት ሳይስፋፋ ቆይቶ ነበር። ከዚያ በኋላ ግን ሚሊዮኖች ጊዜያቸውን እና ጉልበታቸውን ስለሚቆጥብ በፈለጉት ጊዜ እና ባሉበት ቦታ በቀላሉ ገንዘብ ለመላክ፣ የአየር ሰዓት ለመሙላት እና የተለያዩ የአገልግሎት ክፍያዎችን ለመፈጸም ተጠቅመውበታል። የባንካችን ደንበኞች የሆኑ የተለያዩ ተቋማትም የአገልግሎት ክፍያዎቻቸውን በቀላሉ እና በወቅቱ ሰብስበውበታል።

የሲቢኢ ብር አገልግሎት በባንካችን በኩል የሚካሄዱ ጥሬ ገንዘብ አልባ ግብይቶችን በጉልህ መጠን በማሳለጡ ለአብነት ያህል በ2016 የበጀት ዓመት በባንኩ በኩል ከተካሄዱ ግብይቶች መካከል 72 በመቶው የዲጂታል ቻናሎች ድርሻ እንዲሆን የበኩሉን አስተዋፅኦ አበርክቷል። ከ11 ሚሊዮን በላይ ደንበኞች ጥሬ ገንዘብ አልባ ግብይትን አከናውነውበታል። በ10 ሺህ የሚቆጠሩ ወኪሎችን የኮሚሽን ገቢ

አግኝተውበታል፡፡ የአገልግሎቱ መስፋፋት ጠቀሜታ እንደዚህ ከባንኩ እና ከደንበኞቹ አልፎ ለሌሎች አካላት ተርፏል።

ይህም ባንኩ አገልግሎቱን በትኩረት እንዲሠራበት በማበረታታቱ አገልግሎቱ ሰፊ የማሻሻያ ሥራ ተከናውኖበታል። ለዚህ ዋነኞቹ ማሳያዎች ደግሞ ባንኩ በየጊዜው የሚጨምረውን የደንበኞች የፍላጎት ዓይነት ከግምት አስገብቶ በሲቢኢ ብር ፕላስ መተግበሪያ ያካተታቸው የሚከተሉት አዳዲስ ገጽታዎች እና ጠቀሜታዎች ናቸው።

1. ራስን በራስ መዝግቦ አገልግሎቱን ማግኘት፡- ቀድሞ የሲቢኢ ብር አገልግሎት ተጠቃሚ ለመሆን ወደ ባንኩ ቅርንጫፍ ወይም ወኪል መሄድ ያስፈልግ ነበር። በዚህ ወቅት ግን የሲቢኢ ብር ፕላስ መተግበሪያን ከአፕ ስቶር ወይም ከጉግል ፕሌይ ስቶር በማውረድ ራስን በራስ መዝግቦ አገልግሎቱን መጠቀም ተችሏል።
2. ከመደበኛ የባንክ ሒሳብ ጋር የተገናኙ አገልግሎቶችን ማግኘት፡- እነዚህን አገልግሎቶች ለማግኘት በመጀመሪያ ወደ ባንኩ ቅርንጫፍ ሄዶ የሲቢኢ ብር ሒሳብን ከመደበኛ የባንክ ሒሳብ ጋር ማስተሳሰር ያስፈልጋል። ከዚያ በኋላ በሲቢኢ ብር ፕላስ መተግበሪያ አማካይነት ከመደበኛው የባንክ ሒሳብ ወደ ሲቢኢ ብር ሒሳብ ገንዘብ መሳብ፣ ገንዘብ መላክ፣ የነዳጅ ክፍያ መፈጸም፣

ማንኛውንም የግብይት ክፍያ መፈጸም እና የአገልግሎት ክፍያዎችን መፈጸም ይቻላል።

3. የማጂክ ፔይ አገልግሎትን ማግኘት፡- ማጂክ ፔይ አገልግሎት አንድ የሲቢኢ ብር ፕላስ መተግበሪያ ተጠቃሚ በአቅራቢያው ላለ ግለሰብ ገንዘብ መላክ ሲፈልግ፣ ላኪው የQR ኮድ አዘጋጅቶ ተቀባዩ በመተግበሪያው እንዲያነብበው በማስደረግ ገንዘብ እንዲልክ ማድረግ ያስችላል።

4. የታቀደ ክፍያ መፈጸም፡- የሲቢኢ ብር ፕላስ መተግበሪያ አስቀድሞ በታቀደለት መሠረት ራሱ ገንዘብ መላክ እና የአየር ሰዓት መሙላት ይችላል። የተለያዩ የአገልግሎት ክፍያዎችን ደግሞ በታቀደለት መሠረት ደንበኛው እንዲከፍል ያስታውሳል።

5. የኮንዶሚኒየም ብድር ክፍያ መፈጸም፡- ቀድሞ ቅርንጫፍ በመሄድ ብቻ ይፈጸም የነበረውን የኮንዶሚኒየም ቤት የብድር ክፍያ የሲቢኢ ብር ፕላስ መተግበሪያን በመጠቀም ብቻ በማንኛውም ጊዜ ካሉበት ቦታ ያለ እንግልት በወቅቱ መክፈል ይቻላል።

6. የሒሳብ ደኅንነትን በባዮሜትሪክ ዘዴ ማረጋገጥ፡- ቀደም ሲል የሲቢኢ ብር ሒሳብን ደኅንነት ለማረጋገጥ የይለፍ ቁጥር (PIN) ብቻ የሚጠየቅበት አሠራር ነበር። የሲቢኢ ብር ፕላስ መተግበሪያ ግን ደንበኞች የባዮሜትሪክ (የእጅ አሻራ ወይም የፊት ገጽ መለያ) በመጠቀም የሒሳባቸውን ደኅንነት ይበልጥ እንዲያረጋግጡ ያስችላል።

7. መገኛ ስፍራን ማወቅ፡- የሲቢኢ ብር ፕላስ መተግበሪያን በመጠቀም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ኤቲኤሞች፣ ወኪሎች፣ አጋር ነጋዴዎች እና አገልግሎቱን የሚጠቀሙ የነዳጅ ማደያዎች የሚገኙበትን ስፍራ ማወቅ ይቻላል።

8. የቅርብ ጊዜ ግብይቶችን ደረሰኝ ማውረድ ወይም ማተም፡- በሲቢኢ ብር አገልግሎት ግብይት የፈጸመ ተጠቃሚ ለቅርብ ጊዜ ግብይቶቹ ደረሰኝ መያዝ ቢያስፈልገው፣ ደረሰኞቹን በመተግበሪያው አማካይነት በዲጂታል መልክ ማተም ወይም ዲጂታል ደረሰኞቹን በወረቀት ማተም ይችላል።

የሲቢኢ ብር ፕላስ መተግበሪያን ለማስተዋወቅ ሲቢኢ ብር ፕላስ ኤክስፖ መልካም አጋጣሚ ፈጥሯል፡፡

9. በሲቢኢ ብር መተግበሪያ ላይ በተጫኑ ሚኒ አፕስ አማካይነት ለሚታዩ አቅርቦቶች ክፍያ መፈጸም፡- የሲቢኢ ብር ፕላስ መተግበሪያ ሚኒ አፕስን (የሌሎች ምርት እና አገልግሎት አቅራቢ ድርጅቶች መተግበሪያዎችን) ስለሚጭን የድርጅቶቹን አቅርቦቶች ከመተግበሪያው ሳይወጡ ማግኘት ያስችላል። በዚህም ምክንያት ሲቢኢ ብር ፕላስ ፈቅዶ ባስቀመጣቸው መተግበሪያዎች አማካይነት ለገበያ የቀረቡ ምርቶችን እና አገልግሎቶችን መርጦ በመተግበሪያው አማካይነት ተገቢውን ክፍያ በመፈጸም መገበያየት ይቻላል።

10. ሌሎች አገልግሎቶችን ማግኘት፡- የሲቢኢ ብር ፕላስ መተግበሪያ የአየር ሰዓት እና የኢንተርኔት ዳታ ጥቅሎችን ለመግዛት ይውላል። ገንዘብን በአንድ ጊዜ እስከ 5 ለሚደርሱ ሰዎች በቡድን መላክም ያስችላል። በተጨማሪም ገንዘብን ወደ ሌላ ባንክ ሒሳብም ሆነ ወደ ሌሎች ዋሌቶች ለማስተላለፍ ያገለግላል። ገንዘብ ለመለገስ የሚፈልጉ ደንበኞች እንዲጠቀሙበት ሆኖም ተዘጋጅቷል። የኢንተርኔት አገልግሎት በማይኖርበት ጊዜ ደግሞ ወደ *847# መደወል ሳያስፈልግ መተግበሪያው ላይ ሆኖ የሲቢኢ ብር አገልግሎትን ለማግኘት ያስችላል።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሲቢኢ ብር ፕላስ መተግበሪያ እነዚህን ሁሉ ማሻሻያዎች በማካተቱ የተለያዩ የደንበኞች ፍላጎቶችን ለማሟላት እና ዘመኑን የዋጀ አገልግሎት ለማቅረብ የሄደበትን ረጅም ርቀት አሳይቷል። ወደፊትም አገልግሎቱን ይህ ቀረው የማይባል ለማድረግ አብልጦ እንደሚተጋ እሙን ነው። አገልግሎቱ በየጊዜው ዘመኑ የደረሰበትን የእጅ ስልክ ገንዘብ አገልግሎት ደረጃ አሟልቶ በተወዳዳሪነት ቢዘልቅ፣ ባንኩ ብቻ ሳይሆን ደንበኞች እና የግብይት ሥርዓቱ በአጠቃላይ ተጠቃሚዎች ስለሚሆኑ፣ ባንኩ በየጊዜው ለሚፈጠሩ የፋይናንስ እና ተያያዥ የአገልግሎት ፍላጎቶች ተግባራዊ ምላሽ መስጠቱን ይቀጥላል።

ዲጅታል ባንክ - ለመጪው ጊዜ!

በተመስገን ዳምጠው

ዲጂታል የባንክ አገልግሎት በኢትዮጵያ ተግባራዊ መሆን ከጀመረ ዓመታት አልፈዋል፡፡ ዘርፉ በፍጥነት በማደግ ላይ ይገኛል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የዲጂታል ባንክ ም/ፕሬዝዳንት ከሆኑት አቶ ወጋየሁ ገ/ማርያም ጋር የቃለ መጠይቅ ቆይታ አድርገናል። እንደሚከተለው ተጠናቅሯል፡፡ ለቃለ መጠይቁ ስለተባበሩን እናመሰግናለን፡፡ (አቶ ወጋየሁ ገ/ማርያም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በማኔጅመንት የመጀመሪያ ዲግሪ ያገኙ ሲሆን ከሊንከን ዩኒቨርሲቲ (Lincoln University) ደግሞ በንግድ አስተዳደር (MBA) አላቸው፡፡ ላለፉት 28 ዓመታት በኢ.ን.ባ አገልግለዋል፡፡ በባንኩ በተለያየ የሀላፊነት ደረጃዎች የሰሩ ሲሆን አሁን ደግሞ የዲጅታል ባንክ ዲቪዥን ም/ፕሬዘዳንት ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ፡፡)

መልካም ንባብ!

ዐውደ ነዋይ፡- ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የባንካችን የዲጂታል ባንክ አገልግሎት አፈጻጸም እድገት አሳይቷል። የተገኘውን ስኬት ለማስቀጠል ምን እየተሠራ ነው?

ባንካችን በዲጂታል ባንክ አገልግሎት ዘርፍ ስኬት ሊጎናጸፍ የቻለው ለአገልግሎቱ ግልጽ ርእይ አስቀምጦና ስልታዊ ፍኖተ ካርታ ቀርፆ ሥራ በመጀመሩ ስለሆነ መነሻችንን እና መድረሻችንን ዐውቀን እየሠራን እንገኛለን። የባንካችን የመጪ ጊዜ የመወዳደር ዐቅም የሚወሰነው በዚህ ዘርፍ በሚኖረን ተወዳዳሪነት መሆኑን በመገንዘብም በውስጥ ዐቅም ከምንሠራቸው ሥራዎች በተጨማሪ ከ3 ዓመት በፊት መኬንዚ (McKinsey) የሚባል ዓለማቀፍ አማካሪ ድርጅት ያቀረበልንን ምክረ ሐሳቦች ደረጃ በደረጃ ተግባራዊ እያደረግን እንገኛለን። አሁን ላይ ደግሞ PWC ከሚባል ሌላ ዓለም አቀፍ አማካሪ ድርጅት ጋር በመሥራት አገልግሎትን መሠረት ያደረገ ራሱን የቻለ የዲጂታል ባንክ ስትራቴጂ እያዘጋጀን እንገኛለን።

በተጨማሪም ከ45 ሚሊዮን በላይ ከሆኑት የባንካችን ሒሳብ ተጠቃሚዎች መካከል የዲጂታል ባንክ አማራጮችን የሚጠቀሙትን ቁጥር ለማሳደግ እየሠራን ነው። እንዲሁም አዳዲስ ተጠቃሚዎችን የማምጣት ሥራ እያከናወንን እንገኛለን፡፡ በተመሳሳይም በዚህ ወቅት ያሉንን መደበኛ የዲጂታል ባንክ አገልግሎት ቻናሎች በመጠቀም ከምንሰጣቸው የተለያዩ አገልገሎቶች በተጨማሪ አዳዲስ አገልግሎቶችን በየጊዜው እናስተዋውቃለን። ያሉንን ቻናሎች ወይም መተግበሪያዎች የማበልጸግ ሥራዎችንም እንሠራለን። ለምሳሌ፣ በቅርቡ በሲቢኢ ብር አገልግሎታችን

አቶ ወጋየሁ ገ/ማሪያም
የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዲጂታል ባንክ - ም/ፕሬዚደንት

ላይ በውስጥ ዐቅም በርካታ የማሻሻያ ተግባራትን አከናውነን መተግበሪያውን 'ሲቢኢ ብር ፕላስ' በሚል ስያሜ በአዲስ መልክ አስተዋውቀናል። የዲጂታል ባንክ አገልግሎቶቻችን 24\7 አስተማማኝ የሆነ እና ያልተቆራረጠ አገልግሎት እንዲሰጡ ደግሞ ጠንካራ የክትትል ሥራዎችን ከማከናወን ባሻገር ከደንበኞች የሚቀርቡ ቅሬታዎችና ጥያቄዎች ካሉ ለመፍታት የሚያስችል ሥርዓት ፈጥረን በመጠቀም ላይ እንገኛለን።

ዐውደ ነዋይ፡- ዲጂታል የባንክ አገልግሎቶች በአገር አቀፍ ደረጃ በስፋት እየተለመዱና በመስኩ የሚደረገው ውድድርም እየከረረ መጥቷል። በዚህ ረገድ የባንካችን ዝግጅት ምን ይመስላል?

የምንወዳደረው ከባንኮች ጋር ብቻ አይደለም! በዲጂታል የባንክ አገልግሎት

ዘርፍ ባንክ ያልሆኑ ተቋማትም ጭምር እንደሚንቀሳቀሱ ይታወቃል። ባንካችን የዚህን አገልግሎት ዕምቅ ኃይል ቀድሞ በመረዳት ከሁሉም ባንኮች በፊት ነው ዲቪዥን አዋቅሮለት እንዲመራ ማድረግ የጀመረው። አደረጃጀቱም ዘርፉ ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ በዋና መ/ቤት ብቻ ሳይወሰን ወደ ቀጣና ጽ/ቤቶች፣ የዲስትሪክት ጽ/ቤቶች እና ቅርንጫፎች ወርዶ ነው የተዋቀረው፡፡

በተጨማሪም ባንካችን በየዓመቱ ትልቅ የካፒታልና የኦፐሬሽን በጀት መድቦ ሥራ ላይ በማዋል አዳዲስ አሠራሮችንና ቴክኖሎጂዎችን ለገበያው ያስተዋውቃል። ለአብነትም፣ በቅርቡ በፊት የነበሩትን የፖስ ማሽኖች ወደ ስማርት ፖስ ማሽኖች ቀይሮ ንክኪ አልባ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ኤቲኤሞችን እና የፖስ ማሽኖችን ወደ ገበያው አስገብቷል።

በሌላም በኩል ደንበኞች የኤቲኤም ካርድ ለማግኘት ከቅርንጫፍ እስከ ዋና መ/ቤት ያስፈጽሙ የነበረውን ሂደት በማስቀረት ካርዱ ወዲያውኑ ታትሞ እንዲሰጣቸው የሚያስችል ማሽን እየተጠቀመ አገልግሎቱን በተመረጡ ትልልቅ ቅርንጫፎች በመስጠት ላይ ይገኛል። በተጨማሪም ቦሌ አካባቢ አንድ ስማርት ቅርንጫፍ ያቋቋመ ሲሆን፣ በተመሳሳይ ሌሎች 5 ቅርንጫፎችን የመክፈት እንቅስቃሴ እያደረገ ነው። ሌሎችም በኢንዱስትሪው መሪ የሆነባቸው አገልግሎቶች አሉት፤ ለአብነትም፣ ማየት ለተሳናቸው ወገኖች በድምፅ የታገዘ የኤቴኤም አገልግሎት የሚሰጥበትን አማራጭ ለገበያው አስተዋውቋል።

ዓለም አቀፍ መልካም ተሞክሮ እንደሚያሳየው የዲጂታል ባንኪንግ እድገትን ለማስቀጠል ከሌሎች ተቋማት ጋር በቅንጅት መሥራት ስለተለመደ ባንካችን በአንጻራዊነት ጥሩ ዐቅም ካላቸው የፊንቴክ ኩባንያዎች (Fin-techs) ጋር በመተባበር ለደንበኞቹ ምቹና ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት የሚያስችሉ ሥራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል። አብዛኞቹን የዲጂታል ባንክ አገልግሎቶቹን ሌሎች ተመሳሳይ ተቋማት ከባንካችን እያዩ ተግብረዋቸዋል፡፡ ይህም የሚያመላክተን ባንካችን በዲጂታል ባንክ አገልግሎት ዘርፍ የገበያ ውድድሩን በብዙ ርቀት እየመራ እንደሆነና በቀጣይም መሪነቱን አስጠብቆ እንደሚቀጥል ነው፡፡

ዐውደ ነዋይ፡- የባንካችን የዲጂታል የባንክ አገልግሎት አማራጮች ለደንበኞች ያላቸውን ምቹነት እንዴት ይገልጹታል?

የዲጂታል ባንክ አገልግሎት ዋና ጠቀሜታ ደንበኞች ባመቻቸው ጊዜና ቦታ አገልግሎቱን ራሳቸው ጀምረው እንዲጨርሱ ማስቻሉ ነው፡፡ ስለሆነም

> የምንወዳደረው ከባንኮች ጋር ብቻ አይደለም! በዲጂታል የባንክ አገልግሎት ዘርፍ ባንክ ያልሆኑ ተቋማትም ጭምር እንደሚንቀሳቀሱ ይታወቃል። ባንካችን የዚህን አገልግሎት ዕምቅ ኃይል ቀድሞ በመረዳት ከሁሉም ባንኮች በፊት ነው ዲቪዥን አዋቅሮለት እንዲመራ ማድረግ የጀመረው።

አገልግሎቶቻችን ለአጠቃቀም ቀላልና ምቹ ከመሆን ባለፈ የደንበኞችን ፍላጎትና የመጠቀም ችሎታ መሠረት ባደረገ መልኩ ይቀርባሉ። በደንበኞች አስተያየቶች መሠረትም የማሻሻያ ሥራዎችን እናከናውናለን። ስለዚህም የዲጂታል ባንክ አገልግሎቶቻችን እንደ ደንበኞች ምርጫ በተለያየ ቋንቋ የቀረቡ፣ ለእይታ ማራኪና ሳቢ ቻናሎች ያሏቸው እና ባለሙያዎች ደንበኞች እየተጠቀሟቸው እንዲቆዩ ለማድረግ የተጠበቡባቸው ናቸው። ከአስተማማኝነት አንጻርም፣ ቻናሎቹ ደንበኞች በእያንዳንዱ ሂደት ወይም ቅደም ተከተል ከማንኛውም የደኅንነት ሥጋት ነጻ ሆነው እንዲጠቀሙባቸው የተዘጋጁ ናቸው ማለት እንችላለን፡፡

ከአመችነት ጋር በተያያዘ፣ ባንካችን ራሱ ያበለጸገው ኢትዮ-ዳይሬክት (EthioDirect) የሚባል የውጪ ሐዋላ መላኪያ መተግበሪያ እና ከአጋሮቹ ጋር እየሠራበት የሚገኘው ካሽጎ (Cash-Go) የሚባል አማራጭ የገንዘብ መላኪያ አገልግሎቶች ተጠቃሽ ናቸው። እነዚህ አገልግሎቶች በተለይ የሀገራችን የውጭ ምንዛሬ አስተዳደር በገበያው ሥርዓት እንዲመራ ከተደረገ በኋላ ከውጭ ሀገር ገንዘብ ለሚልኩ ሰዎች ምቹና ቀልጣፋ አማራጮች እንዲሆኑ ውጤታማ ማሻሻያ ተደርጎባቸዋል። በተጨማሪም አርሶ አደሮች የማዳበሪያ ክፍያቸውን በዲጂታል



የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዲጂታል ባንክ ቅርንጫፍ (ቦሌ መንገድ)

መንገድ እንዲፈጽሙ ለማስቻል ከኦሮሚያ ክልል መንግሥት ጋር በሙከራ ደረጃ በመሥራት ላይ እንገኛለን።

ዐውደ ነዋይ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዲጂታል የባንክ አገልግሎቶች ተደራሽነት ምን ይመስላል?

የባንካችን ዲጂታል የባንክ አገልግሎት ተደራሽነት በከፍተኛ ፍጥነት በማደግ ላይ ይገኛል፡፡ በሁሉም መመዘኛዎች ማለት በሚያስችል ደረጃ የኢንዱስትሪው ከግማሽ በላይ የገበያ ድርሻ የባንካችን ነው። የባንካችን መረጃ እንደሚያመላክተው፣ የኤቲኤሞቻችን ቁጥር 3,858፣ የፖስ ማሽኖቻችን ቁጥር 5,300 አካባቢ፣ የሞባይል ባንክ አገልግሎታችን ተጠቃሚዎች ቁጥር ከ10 ሚሊዮን በላይ፣ የክፍያ ካርዶቻችን ተጠቃሚዎች ቁጥር 21 ሚሊዮን ያህል፣ የሲቢኢ ብር አገልግሎታችን ተጠቃሚዎች ቁጥር ደግሞ 30 ሚሊዮን ደርሷል። የአገልግሎቱ ተደራሽነት ይህን ያህል በማደጉም፣ ባንካችን በያዝነው በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት 402 ሚሊዮን ግብይቶችን ወይም ከአጠቃላይ ግብይቶች 80% ያህሉን በዲጂታል አማራጮች አስተናግዶ ነበር።

ዐውደ ነዋይ፡- የባንካችን የዲጂታል ባንክ አገልግሎት የደኅንነት ጥበቃና አስተማማኝነት እንዴት ይገለጻል?

ሁሉም ዲጂታል የባንክ አገልግሎቶቻችን የሚጠበቅባቸውን ደረጃ ያሟሉ፣ በአገር አቀፍ የባንክ ኢንዱስትሪው ተቆጣጣሪ

ባንካችን በያዝነው በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት 402 ሚሊዮን ግብይቶችን ወይም ከአጠቃላይ ግብይቶች 80% ያህሉን በዲጂታል አማራጮች አስተናግዶ ነበር።

አካላት የደኅንነት ፍተሻ ተደርጎባቸው ያለፉ እና ባንኩ ባስቀመጣቸው መለኪያዎች በባለሙያዎች ተፈትሸው የደኅንነታቸው አስተማማኝነት የተረጋገጠ ናቸው። እንዲሁም አገልግሎቶቻችን በዓለም አቀፍ ደረጃ መለኪያ (ISO 27001\22 Certification for Information Security Management for People, Process and Technology) እና በክፍያ ካርድ ኢንዱስትሪ የመረጃ ደኅንነት መለኪያ (Payment Card Industry Data Security Standard) ተፈትሸው የደኅንነት ማረጋገጫ ተሰጥቶናል።

በተጨማሪም ለባንካችን የዲጂታል ባንክ አገልግሎት ቻናሎች እና አገልግሎቶች ተብሎ የተቋቋመ እና በተለየ ሁኔታ የሠለጠነ የባለሙያዎች ቡድን በቴክኖሎጂ ታግዞ 24\7 የአገልግሎት ጥራት የመቆጣጠር ሥራ ያከናውናል። በተመሳሳይም የአገልግሎቱ የዝውውር እንቅስቃሴዎች በሳይበር ደኅንነት ሥራ ማእከል ቡድን 24\7 ክትትል ይደረግባቸዋል። ይህንን የሚያጠናክር ተከታታይነት ያለው የሠራተኞች ሥልጠና እና ግምገማ እየተካሄደም የሰው ኃይሉን የማብቃት ሥራ ይከናወናል። እንግዲህ ከእነዚህ መመዘኛዎች አንጻር ስንመለከተው የባንካችን ዲጂታል የባንክ አገልግሎት የደኅንነት ጥበቃ አስተማማኝ ቁመና ላይ መሆኑን አስረግጠን መናገር እንችላለን፡፡

ዐውደ ነዋይ፡- በሀገር አቀፍ ደረጃ ዲጂታል የባንክ አገልግሎት እንዳይስፋፋ የሚያጋጥሙት ተግዳሮቶች ምን ምን ናቸው?

በዋናነት እንደ ተግዳሮት የምንወስደው የኢንተርኔት ሽፋን እና አቅርቦት ከዋና ዋና ከተሞች ባለፈ በሁሉም የሀገራችን ክፍሎች በሚፈለገው መጠን ወይም በተሟላ ሁኔታ አለመቅረቡን ነው። ሌላው ተግዳሮት የኅብረተሰቡ ዲጂታል የባንክ አገልግሎትን የመጠቀም ዝንባሌ ምንም እንኳ እድገት በማሳየት ላይ ያለ ቢሆንም፣ በባንካችን ግምገማ መሠረት በቂ አለመሆኑ ነው። የኅብረተሰቡን አጠቃቀም ስንመለከት፣ አገልግሎቱን ከጅምሩ የማይጠቀሙ፣ ጀምረው በተለያየ ምክንያት ያቋረጡ እና/ወይም በጣም ለተወሰነ ዓላማ (ለምሳሌ የአየር ሰዓት ለመግዛት ወይም የውኃና

የመብራት አገልግሎት ክፍያ ለመፈጸም ብቻ) የሚጠቀሙ ደንበኞች አሉ።

ከሌሎች ተቋማት ጋር በመሥራት ረገድም ክፍተት አለ። በሌሎች አገሮች ባንኮች በተወሰነ መልኩ ከፊንቴኮችና ከተለያዩ ተቋማት ጋር አጋርነት በመፍጠር ሥራን ያሳልጣሉ እንጂ ሁሉንም የዲጂታል ባንክ አገልግሎት እና የሳይበር ደኅንነት ሥራዎች ብቻቸውን አያከናውኑም፡፡ ወደ አገራችን ስንመጣ ግን፣ በሚፈለገው ልክ ብቃት ያላቸውና በቁጥርም በርከት ያሉ ፊንቴኮችና መፍትሔ አቅራቢዎችን ማግኘት አስቸጋሪ በመሆኑ፣ ባንካችን ካሉት ፊንቴኮች ጋር ብቻ ለመሥራት የተገደደበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡ በአንጻራዊነት አነስተኛ በሚባሉ ዲጂታል ግብይቶች ላይ አልፎ አልፎ የሚፈጸም የማጭበርበርና የስርቆት ተግባርም አገልግሎታችንን ይፈትናል፡፡ ደንበኞቻችንን ለይተን የምናውቅበት አንድ መለያ መታወቂያ በስፋት ተግባራዊ አለመደረጉን ከዚሁ ከማጭበርበር ተግባር ጋር በተያያዘ እንደ ተግዳሮት እንወስደዋለን፡፡

ዐውደ ነዋይ፦ ዲጂታል የባንክ አገልግሎት ለአህጉራችን አፍሪካ የኢኮኖሚ እድገትን ከማሳለጥ አንጻር የሚያበረክተው አስተዋፅኦ ምንድነው?

ዲጂታል ቴክኖሎጂ (Digitalization) አፍሪካ እስካሁን ወደኋላ የቀረችበትን የእድገት መጠን አካክሳ ወደፊት የምትራመድበትን ትልቅ አማራጭ ስለፈጠረ ዘርፉን እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ከኋላ ቀርነት ተላቅቃ ወደ እድገት ማማ ልትሸጋገር ትችላለች፡፡ በአፍሪካም ሆነ በተለይ በምሥራቅ አፍሪካ ብዙውን ጊዜ መሠረተ ልማት በበቂ ሁኔታ ባልቀረበበት ሁኔታ የተሟላ መደበኛ የፋይናንስ አገልግሎት ማቅረብ ያስቸግራል። በዚህ ረገድ ዲጂታል ቴክኖሎጂው እንደ ቁጠባ፣ ብድር፣ ክፍያና ገንዘብ ማስተላለፍ የመሳሰሉ የፋይናንስ አገልገሎቶችን የመደበኛው የባንክ አገልግሎት አማራጮች ከሚወስዱት ባነሰ ጊዜና ወጪ በማቅረብ የደንበኞችን እርካታ ከፍ ማድረግ ያስችላል።

ቴክኖሎጂው የሥራ ዕድል በመፍጠር ረገድም ቀላል የማይባል አስተዋፅኦ በማበርከት ላይ ይገኛል። ባንካችንን ለአብነት ብናይ፣ ወኪሎቹ ሆነው በመሥራታቸው ተጠቃሚ የሆኑ ወገኖች አሉ። የዲጂታል ባንክ አገልግሎት እድገት ይበልጥ በተፋጠነ መጠን፣ ወጪን ከመቀነሱም በላይ ከአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችም ሆነ ከሌሎች ዘርፎች የሚገኘው ገቢ በዚያው መጠን ያድጋል። እነዚህ ሁሉ ተጠቃልለው ተጨማሪ ገቢን በመፍጠር እና አጠቃላይ ኢኮኖሚውን በማሳደግ ለአፍሪካ ሀገራት ጠቅላላ ምርት (GDP) በጎ አስተዋፅኦ በማበርከት ላይ ይገኛሉ።

ዐውደ ነዋይ፦ "ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025" አገራዊ ዕቅድን ከማሳካት አኳያ የባንካችን ሚና ምን ሊሆን ይችላል ይላሉ?

ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 አገራዊ ዕቅድ በጥቅሉ ስንመለከተው በአራት ዋና ዋና ምሶሶዎች ላይ የቆሙ አራት ክፍሎችን ለይቶ አስቀምጧል። እነሱም ዲጂታል አገልግሎትን ለግብርና፣ ዲጂታል አገልግሎትን ለአምራች ኢንዱስትሪው፣ ዲጂታል አገልግሎትን ለመረጃ ቴክኖሎጂ እና ዲጀጂታል አገልግሎትን ለቱሪዝም ናቸው፡፡ ባንካችን "ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025" ሀገራዊ ዕቅድ እውን እንዲሆን ከማድረግ አንጻር በሁሉም መስኮች ቀላል የማይባል ሚና እንዳለው ይታወቃል፡፡ በዋናነት ግን የመረጃ ቴክኖሎጂን በማነፅና በማብቃት ዘርፍ ትልቅ አበርክቶ እየሰጠ ይገኛል፡፡

በዚህ ዘርፍ ውስጥ ከተካተቱት መካከል ለአብነት ዲጂታል መታወቂያን ስንመለከት፣ ባንካችን በተናጠልና በባንኮች ማኅበር አማካይነት የሚሠራቸው ሥራዎች አሉ፡፡ የዲጂታል መታወቂያ ፕሮግራሙ ሲጀመር አንሥቶ በቅርንጫፎች በኩል አገልግሎቱ እንዲሰጥ ከማድረግ ባለፈ፣ በባንኩ ደረጃ መሸፈን ያለባቸው ወጪዎች ሲኖሩ ሸፍነናል። ከተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ጋርም የክፍያ አፈጻጸምን በማሳለጥ ረገድ አብረን በመሥራት ላይ እንገኛለን። በርካታ የግል ተቋማት ከባንካችን ጋር በመሥራት ላይ ሲሆኑ፣ የመንግሥት ተቋማት በፌደራልም ሆነ በክልሎች ደረጃ የሚጠቀሙበትን የግብር ክፍያ አግልግሎት ለማቀላጠፍ ክፍያቸውን በኢንተርኔት የባንክ አገልግሎታችን እና በሲቢኢ ብር አገልግሎታችን እንዲፈጽሙ እያደረግን ነው፡፡

ባንካችን ከዚህ ቀደም ዜጎች በስፋት የሚጠቀሙባቸው የፓስፖርት፣ የመብራት፣ የውኃና የመሳሰሉ የአገልግሎት ክፍያዎች ሲፈጸሙ ይደርስ የነበረውን መጉላላት በእጅጉ ለመቀነስ ዲጂታል የክፍያ አማራጮችን በማቅረብ ረገድ የመሪነትን ሚና በመጫወት ላይ ይገኛል፡፡ ኤሌክትሮኒክ ንግድ (E-commerce) በሕግ ማእቀፍ ተደግፎ ወደ መደበኛ እንቅስቃሴ ሲገባም በሙሉ ዐቅምና ተነሣሽነት ሥራዎችን ለማከናወን ተዘጋጅቷል፡፡ በአጠቃላይ ስንመለከት ሀገራዊው የዲጂታል ጉዞ ርእይ እውን እንዲሆን ትልቅ አስተዋፅኦ እያረገ ነው ማለት እንችላለን፡፡

አገር ወካዮች መፍለቂያ፤ ሻምፒዮናነት መድመቂያ!

በምንተስኖት አስቻለው

ግዙፉ ስታዲየም - ስታድ ደ ፍሯንስ በሺዎች በሚገመቱ የአትሌቲክስ አፍቃሪዎች ደምቋል፡፡ በተለያዩ ቀለማት የተሸቆጠቆጡ ደጋፊዎች በስታዲየሙ ዙሪያ ተኮልኩለዋል፡፡ በርካቶች የየአገራቸውን ሰንደቅ እያውለበለቡ ተወካዮቻቸውን ያበረታታሉ፡፡

በፍጥነትና በተከታታይነት የሚካሄዱት ስፖርታዊ ክንዋኔዎች ገሚሱን እያስፈነደቁ ቀሪውን እያስቆጩ ስታዲየሙን በድራማዊ ትዕይንቶች ሞልተውታል፡፡

በዕለቱ መርሐ - ግብር መሠረት ፍጻሜውን የሚያገኘው የሴቶች 800 ሜትር ውድድር በብዙዎች ዘንድ በጉጉት ተጠባቂ ነው፡፡ የዓለማችን ምርጥ እንስት አትሌቶች የውድድሩ ተፋላሚዎች ናቸው፡፡

የስታዲየሙ ድምፅ ማጉያዎች ተወዳዳሪ

አትሌቶችን ማስተዋወቅ ጀመሩ፡፡

በደጋፊዎች ጭብጨባና ረብሻ የታጀቡት አትሌቶቹ ቦታቸውን ያዙ፡፡ ሚሊዮኖች ከያሉበት ሆነው ከቴሌቪዥን መስኮቶቻቸው ስር ተሰለፉ፡፡ በስቴዲየሙ ያሉ ዓይኖች ሁሉ በመሮጫው መም ላይ አፈጠጡ፡፡ የስታዲየሙ ጆሮዎች አንድ ድምፅ ለመስማት ተቀሰሩ፡፡

‹‹ኳ!››

ውድድሩ ተጀመረ፡፡ አንድ ደቂቃ ከ56 ሴኮንዶች ...፤ የአትሌቶቹ ቀልጣፋ እግሮች የውድድሩን ማጠናቀቂያ መሥመር ተሻገሩ፡፡ አንደኛ...፣ ሁለተኛ!... ተጠናቀቀ፡፡

አዲስ ክሥተት በኦሎምፒክ ታሪክ ተጻፈ፡፡

‹‹ኢትዮጵያ!›› የሚል ድምፅ ተከታትሎ ተሠማ፡፡

‹‹ብር ለኢትዮጵያ!››

አትሌት ጽጌ ዱጉማ! የአገሯን ሰንደቅ ከትከሻዋ ደርባ በስቴዲየሙ ተንጎራደደች፡፡ ትንፋሿ ድካሟን ቢያሳብቅም፤ እንደ ጥጥ ባዘቶ በነጧጡ ጥርሶቿ ፈቷ በርቶ፤ ፈገግታዋ ስታዲየሙን አሞቀው፡፡ ኢትዮጵያ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ በኦሎምፒክ መድረክ በ800 ሜትር ውድድር የብር ሜዳሊያ አገኘች፡፡

ኃፍታም ሳይቆይ የዓለም እና የአገር ውስጥ ብዙሀን መገናኛዎች ድሉን ተቀባበሉት፡፡ ‹‹የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ስፖርት ክለብ ፍሬ የሆነችው ጽጌ ዱጉማ ለአገሯ በ800 ሜትር የብር ሜዳሊያ በማግኘት አዲስ ታሪክ ጻፈች፡፡››

እንደ አትሌት ጽጌ ዱጉማ ሁሉ የአገራችንን ሰንደቅ በዓለም አደባባይ ከፍ ያደረጉ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አትሌቶችና ስፖርተኞች በርካታ ናቸው፡፡

ባጠናቀቅነው 2016 ዓ.ም. ውድድር ዘመን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ስፖርት ማኅበር በአትሌቲክስ፣ በጠረጴዛ ቴኒስ፣ በሴቶችና ወንዶች እግር ኳስ ቡድኖቹ ስኬታማ ምዕራፍ አሳልፏል፡፡

ማኅበሩ በአገር ውስጥ እና ውጪ አገር በተሳተፈባቸው ስፖርቶች ሁሉ ጠንካራና የማይበገር ተፎካካሪ ሆኖ አጠናቋል፡፡ በአጠቃላይ በአገር ውስጥ ከተካሄዱ ውድድሮች 37 ዋንጫዎች፣ 91 የወርቅ ሜዳሊያዎች፣ 62 የብር ሜዳሊያዎችና 44 የነሐስ ሜዳሊያዎችን አግኝቷል፡፡

> ባንካችን በፋይናንስ ዘርፉ ቀዳሚ እንደሆነው ሁሉ፤ በስፖርቱም ዘርፍ ቀዳሚ መሆን አለበት።

የስፖርት ማኅበሩ የበላይ ጠባቂና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፕሬዚደንት አቶ አቤ ሳኖ እንደሚናገሩት ባንኩ በማኅበራዊ ሓላፊነት የሚያከናውነው የስፖርት ዘርፍ ልማት ግቡን እንዲመታ ተገቢው ክትትልና ድጋፍ እየተደረገ ነው፡፡

‹‹ባንካችን በፋይናንስ ዘርፉ ቀዳሚ እንደሆነው ሁሉ፤ በስፖርቱም ዘርፍ ቀዳሚ መሆን አለበት። ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለውን አሠራር ተከትለን በመሥራታችን ባጠናቀቅነው በጀት ዓመት በሁሉም የተወዳደርንባቸው ስፖርት ዘርፎች የላቀ ውጤት አስመዝግበናል፡፡›› ሲሉ ይናገራሉ አቶ አቤ፡፡

አገርን ወክለው ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ውድድሮች ላይ የሚሳተፉ የስፖርት ማኅበሩ ፍሬዎችም ቁጥራቸው እያደገ መጥቷል። የፓሪስ ኦሎምፒክ፣ የዓለም ወጣቶች ሻምፒዮና እና አህጉራዊ ውድድሮች ለዚሁ አስረጅ ናቸው፡፡

‹‹ስፖርት የአገርን ገጽታ ከፍ የማድረግ ኃይል አለው፡፡ ለዚሁ ደግሞ በዲስፒሊን የታነጸ ተተኪ ትውልድ ሊኖር ይገባል፡፡›› አቶ ኤፍሬም መኩሪያ እንደሚያስረዱት፡፡

የጠረጴዛ ኳስ ስፖርት ቡድን

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የጠረጴዛ ኳስ ስፖርት ቡድን ከአንጋፋዎቹ ተርታ በቀዳሚነት የሚሰለፍ ነው፡፡ በአገር አቀፍ የስፖርት መድረኮች ለዘመናት መልካም ስም ያተረፈ ነው።

በ2016 ዓ.ም. የውድድር ዘመን በአዲስ አበባና በኢትዮጵያ ጠረጴዛ ኳስ ፌዴሬሽኖች ደረጃ በተከናወኑ ውድድሮች ተሳትፏል፡፡ በውድድር ዓመቱ በድምሩ 17 ዋንጫዎችን ሰብስቧል።

በአፍሪካ ክለቦች ሻምፒዮና ላይ በአዋቂ ወንዶችና ሴቶች ኢትዮጵያን ወክሎ ውድድሩን ወደ አስተናገደችው አገር - ሊቢያ ተጉዟል፡፡ በአዋቂ ወንዶችና ሴቶች የጠረጴዛ ኳስ ስፖርት የነሐስ ሜዳሊያ አግኝቶ ወደ አገር ቤት ተመልሷል፡፡

የአትሌቲክስ ስፖርት ቡድን

የ2016 ዓ.ም. የውድድር ዘመን ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አትሌቲክስ ቡድን በስኬት የተሞላ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ በአዲስ አበባና በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽኖች አማካኝነት በተዘጋጁ ውድድሮች ላይ በመሳተፍ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በዋንጫ ቁጥር ከፍተኛ የሆነ ውጤት አስመዝግቧል፡፡

የተለያዩ የውድድር መድረኮችን በበላይነት በማጠናቀቅ 18 ዋንጫዎች ተበርክተውለታል፡፡ በ53ኛው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ሻምፒዮና የሶስት ዋንጫዎች ባለቤት ሆኗል፡፡ ከ20 ዓመታት ወዲህ ተይዞ የነበረውን የሻምፒዮናነት ማዕረግ በማስጠበቅ ማስቀጠል ችሏል፡፡

በውድድር ዓመቱ 74 የወርቅ፣ 57 የብር እና 42 የነሐስ ሜዳሊያዎችን ከውድድር መድረኮች ጠራርጎ ወስዷል፡፡

በዓለም አቀፍና አህጉራዊ ውድድሮች ላይ አገራችንን በመወከል የሚሳተፉ አትሌቶችን በማስመረጥ ረገድ ስኬታማ ዓመት አሳልፏል፡፡ በፓሪስ ኦሎምፒክ አገራችንን የወከሉ አራት አትሌቶችን አስመርጧል፡፡ በዓለም ወጣቶች ሻምፒዮና አገራችንን በመወከል ሶስት አትሌቶች ተሳትፈዋል፡፡ በሴቶች 800 ሜትር ለአገራችን የብር ሜዳሊያ፤ እና በ21 ኪ.ሜ. ወንዶች እርምጃ ስድስተኛ ደረጃ ውጤት እንዲመዘገብና በኦሎምፒክ የውድድር መድረክ ለመጀመሪያ ጊዜ ታሪክ እንዲጻፍ ምክንያት የሆኑ አትሌቶችን አበርክቷል፡፡

አቶ አቤ ሳኖ
የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ስፖርት ማኅበር የበላይ ጠባቂ

አቶ ኤፍሬም መኩሪያ
የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ስፖርት ማኅበር ፕሬዚደንት

አቶ ኤፍሬም መኩሪያ የስፖርት ማኅበሩ ፕሬዚዳንትና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሰው ኃይል ም/ፕሬዚዳንት ናቸው፡፡

‹‹የስፖርት ማኅበራትም ለዚሁ ትኩረት ሰጥተው መሥራት ይጠበቅባቸዋል። በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ስኬታማ ነበር ማለት ይቻላል፡፡›› የማኅበሩ ፕሬዚደንት እንደሚያብራሩት፡፡

‹‹የባንካችን ስፖርት ማኅበር በዋናነት የአሸናፊነት ሥነ - ልቦና ያዳበሩ፣ ስፖርታዊ ጨዋነትን የተላበሱ እና ብቃት ያላቸው ተተኪዎችን ማፍራት ላይ አተኩሮ ሠርቷል፡፡ አገርን በዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ የስፖርት መድረኮች ላይ ከፍ ለማድረግ ለዚሁ ዝግጁ ሆኖ አስፈላጊውን ተግብሯል። ስኬቶችም ተገኝተዋል፡፡›› በማለት አቶ ኤፍሬም ይናገራሉ፡፡

ስፖርቱን የሚመሩ በየደረጃው የሚገኙ የማኅበሩ ኃላፊዎች ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው አሰራር እንዲከተሉ መደረጉም ለስፖርት ማኅበሩ ውጤታማነት የድርሻውን አበርክቷል። የክትትልና ግምገማ ሥራዎችም በትኩረት ተከናውነዋል።

‹‹ውጤት ላይ በትኩረት እንሠራለን፡፡ ስፖርተኞቻችንም ሆኑ ባለሙያዎች በሚያመጡት ውጤት ይመዘናሉ። ውጤትን ሊጎዱ የሚችሉ ማናቸውንም ተገቢ ያልሆኑ አካሄዶች አንታገስም፡፡ ለስፖርቱ የምናፈሰው ሀብት ተገቢውን ውጤት እንዲመልስ እንረባረባለን፡፡›› ሲሉ ይገልጻሉ አቶ አቤ ሳኖ፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ስፖርት ማኅበር እያስመዘገባቸው ያሉ ውጤቶች ከባንኩም አልፈው ለአገር ኩራት ወደ መሆን ተሸጋግረዋል፡፡ አገርን በመወከል እየተሳተፈባቸው በሚገኙ ውድድሮች መልካም ስም እና ዝና አትርፏል፡፡ የባንኩን ስም በበጎ ከማስጠራቱም ባሻገር እንደ አገር አዳዲስ ክብረ - ወሰኖችን በማስመዝገብ ላይ ይገኛል፡፡

የሴቶች እግር ኳስ ቡድን

ለሠባት ዓመታት በሻምፒዮንነት ዘልቋል፡፡ በ2016 ዓ.ም. የውድድር ዘመን ቡድኑ 26 ጨዋታዎችን አድርጎ 65 ነጥብ አግኝቷል፡፡ የፕሪሚየር ሊግ ተሳትፎውንም በሻምፒዮንነት ክብር አስቀጥሏል፡፡

በአፍሪካ ክለቦች ሻምፒዮና ላይ ተሳታፊ ለመሆን አገራችን ባስተናገደችው የምስራቅና መካከለኛው አፍሪካ ክለቦች ሻምፒዮና ላይ ተሳትፎ አዲስ ታሪክ አስመዝግቧል፡፡ የሻምፒዮንነት ክብርን በመጎናጸፍ የሴካፋ ዞንን በመወከል በአፍሪካ ክለቦች ሻምፒዮና ላይ ለመሳተፍ የሚያስችለውን ትኬት ቆርጧል፡፡

ይህም በኢትዮጵያ የሴቶች እግር ኳስ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ አገራችንን በመወከል በአፍሪካ ክለቦች ሻምፒዮና ላይ የሚሳተፍ ቡድን እንዲሆን አስችሎታል፡፡

የወንዶች እግር ኳስ ቡድን

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የወንዶች እግር ኳስ ቡድን ዋናው እና ታዳጊ ቡድን ተብሎ ይከፈላል፡፡ የዋናው እግር ኳስ ቡድን በ2016 ዓ.ም. የውድድር ዘመን ለኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ ክስተት ነበር ማለት ይቻላል፡፡ በ30 ጨዋታዎች 64 ነጥቦችን አስመዝግቧል፡፡

በባንኩ ስፖርት ማህበር ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የሻምፒዮናነት ማዕረግ በመጎናጸፍ አዲስ ታሪክ ጽፏል፡፡ ሊጉን በተቀላቀለበት ዓመት ሻምፒዮና በመሆን፤ በፕሪሚየር ሊጉ አዲስ ታሪክ ለማስመዝገብ ችሏል፡፡

ሻምፒዮናነቱን ተከትሎም ለመጀመሪያ ጊዜ አገራችንን በመወከል በአፍሪካ ክለቦች ሻምፒዮና ቅድመ ማጣሪያ ጨዋታዎች ላይ ተሳትፏል፡፡ በነዚህ የውድድር መድረኮችም ጠንካራ ተፎካካሪ በመሆን ቡድኑ መልካም ስም ማግኘት ችሏል፡፡

በእግር ኳሱ መድረክ ተተኪዎችን ለማፍራትም የታዳጊ ወጣቶች እግር ኳስ ቡድኖችን ትኩረት ሰጥቷል፡፡ ከ20 እና 17 ዓመት በታች የ “ሀ”ታዳጊ ቡድኖችን አደራጅቷል፡፡ በሁለቱም የታዳጊ ቡድኖች ውድድሮች ላይ እየተሳተፈ፤ ለተተኪዎች ምቹ መድረክ እየፈጠረ ይገኛል፡፡ ባጠናቀቅነው በጀት ዓመት የውድድር መድረኮች የተመዘገቡ ውጤቶች እንደሚያመላክቱት ሁለቱም የታዳጊ ወጣቶች ቡድኖች ውጤታማ የውድድር ዘመን አሳልፈዋል።

አቶ አቤ ሳኖ - የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፕሬዚደንት፣ በመቄዶንያ የአረጋውያንና አዕምሮ ሕሙማን መርጃ ማዕከል ተገኝተው የማዕከሉን የሥራ እንቅስቃሴ ጎብኝተዋል፡፡

አቶ አቤ ሳኖ - የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፕሬዚደንት፣ የሲቢኢ ብር ፕላስ ኤክስፖ 2016 ዓ.ም. መርቀው ከፍተዋል፡፡ ኤክስፖውን በርካታ የመዲናችን ነዋሪዎች ጎብኝተውታል፡፡ ሲቢኢ ብር ፕላስም የኤክስፖው ታላቅ ድምቀት ሆኖ አልፏል፡፡

በ2016 ዓ.ም. በተከናወኑ ስፖርታዊ ውድድሮች የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ክለቦች የላቀ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ የባንኩ የሥራ ኃላፊዎችም በውድድር ሜዳዎች በመገኘት ቡድናቸውን አበረታተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የ2023/24 በጀት ዓመት ዓመታዊ የሥራ አፈጻፀም ግምገማ ጉባኤ ከ2300 በላይ ተሣታፊዎች ታድመውበታል፡፡ የላቀ አፈጻፀም ያስመዘገቡ ቅርንጫፎችና ዲስትሪክቶችም ዕውቅና ተሠጥቷቸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ደጋፊዎች በ2016 ዓ.ም. በተከናወኑ ስፖርታዊ ውድድሮች ቡድናቸውን በተለያዩ መንገዶች በማበረታታት በስፖርት ሜዳዎች ደምቀው ታይተዋል፡፡

CBE
Birr
ባሉበት ሁሉ አለ!
CBEBirr
Commercial Bank of Ethiopia
Balance (ETB)
Reward (ETB)
QUICK ACCESS
Transaction Detail
Send Money
To CBE Acct
Cash Out
Airtime Package
Scheduled Pay
MagicPay
Pay
Mini Apps
Others
ማጂክ ፔይ
አጠገብዎ ላለ ሰው
በቀላሉ ገንዘብ ለመላክ
የተሻሻለውን የሲቢኢ ብር ፕላስ
መተግበሪያ ያውርዱ ባሉበት ይመዝገቡ
GET IN ON Google Play
Download on the App Store
የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
Commercial Bank of Ethiopia